መጋቢት 24 ቀን 1985 ዓ.ም

**<u>ከመጋቢት 1 እስከ 3/1985 "ስለኢትዮጵያ ሰላም" በሚል ርዕስ የኢትዮጵያን የሽግግር ወቅት ቻርተር የሚጻረሩ ኃይሎች በፓሪስ ከተማ በዘጋጁት ኮንፈረንስ ላይ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ሕብረት ተወካይ ተሳታፊ በመሆን ኮንፈረንሱ ያስለፉቸውን ውሳኔዎች በሚመለከት የደኢሕዴሕ አባልና የተወካዮች ምክር ቤት አባል የሆኑት አምስት ድርጅቶች በወሰዱት አቋም የተነሳ መጋቢት 23 ቀን 1985 ዓ.ም በተወካዮች ምክር ቤት የተላለፈ ውሳኔ</u>**

ከመጋቢት 1 እስከ 3/1985 " ስለኢትዮጵያ ሰላም" በሚል ርዕስ ፀረ ቻርተር ኃይሎች እንዲሁም የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ሕብረት ተወካይ በፓሪስ ከተማ ኮንፈረንስ አካሂደው ሬፅሞ ከእውነት የራቀ ፕሮፓጋንዳ በማሰራጨት በኢትዮጵያ ሕግና ሥርዓት የለም፤ የሽግግሩ ሂደት ተጨናግፎአል፣ የሽግግር መንግሥቱም ዉቿኝና ሰላምና ዲሞክራሲን የማያረጋግጥ ነው ብለዋል። ከዚህም በመነሳት የሚከተለውን ውሳኔ ወስነዋል።

"በሐምሌ ወር 1983 ዓ.ም የተጀመረው የሽግግር ሂደት፤ በአመዘኙ ለዘለቂ ሰላም ሁኔታዎችን ለማመቻቸትና ሀቀኛ ዲሞክራሲያዊ ሂደትን ለማስጀመር ያላስቻለ መሆኑን ግንዘቤ በማድረግ፤ በፓሪስ የተደረገው የኢትዮጵያ ሰላም ኮንፈረንስ የሚከተሉትን ውሳኔዎች አስተላልፏል።

፩ በተቻለ አጭር ጊዜ ውስጥ ፤ ሁሉን አቀፍ የሆነ፣ በኢትዮጵያ የሰላምና እርቅ አገራዊ ኮንፈረንስ እንዲጠራ።

፪ የታቀደው የሰላምና እርቅ ኮንፈረንስ ፍሬያማ እንዲሆን የኢህአዴግ ተሳትፎ አስፈላጊ በመሆኑ፤ የፓሪሱ ኮንፈረንስ ተሳታፊዎች፣ ኢህአዴግ በመጪው ኮንፈረንስ ላይ እንዲሳተፍ አበክረው ይጠይቃሉ።

፫ የመጪውን ኮንፈረንስ ዝግጅት ተከታትሎ ለማስፈጸምና ብሎም የኢትዮጵያ ህዝቦችና የዓለም ህብረተሰብን ድጋፍ ለማስገኘት የሰላምና የእርቅ ኮንፈረንስ አስተባባሪ ኮሚቴ እንዲቋቋም።"

እንዲህ ያለው አባባል የተለመደ ቢሆንም የአሁኑን መግለጫ ከወትሮው ለየት የሚያደርገው የሽግግር መንግሥቱ የተወካዮች ምክር ቤት አባላት የሆኑ አምስት ድርጅቶች

የሚገኙበት የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ሕብረት በኮንፈረንሱ መሳተፉ ነበር።

ቻርተሩንና የሽግግር መንግሥቱን እንደግፋለን በማለት በሽግግር መንግሥቱ ተሳታፊ የሆኑ ድርጅቶች በእንደዚህ ዓይነቱ ተግባር መሰተፋቸው አግባብ አለመሆኑን በማመን ምክር ቤቱ በጉዳዩ ላይ በሰፊው ተወያይቶበት ድርጅቶቹ አቋማቸውን እንዲያብራሩ ጠይቋል።

የከምባታ ሕዝቦች ኮንግሬስ፣ የጉራጌ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ግንባር፣ የወላይታ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር፣ የቡርጂ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት፣ የከፋ አስተዳደር ክልል ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ አንድነት ለምክር ቤቱ በተለመደው ሕጋዊ አቢኋን የሚያቀርቡት ቅሬታ እንዳላቸው ገልፀው ነገር ግን የፓሪሱን መግለጫና ውሳኔ እንደማይቀበሉ አረጋግጠዋል። ምክር ቤቱም የአምስቱንም ድርጅቶች ማብራሪያ ተቀብሏል።

የሲዳማ አርነት ንቅናቄ፣ የኦሞ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ግንባር፣ የሃዲያ ብሔር ዲሞክራሲያዊ ድርጅት፣ የጌድኦ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት፣ የየም ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ፣ የሽግግር መንግሥቱን ሕጋዊነት የሚቀበሉ፣ መፍረሱን የማይደግፉና በፓሪስ ኮንፈረንሱ ላይ የተቀመጡት አንዳንድ ግንዛቤዎችን የማይቀበሉ መሆናቸውን ሲገልፁ በሌላ በኩል ግን የኮንፈረንሱን ውሳኔ እንደሚቀበሉ አረጋግጠዋል። ምክር ቤቱ የኮንፈረንሱን ውሳኔ መቀበል ድርጅቶቹ እንቀበለዋለን የሚሉትን ነገር የሚሸርና በሽግግር መንግሥቱ ውስጥ ያላቸውን አቋም የሚያናጋ መሆኑን በመገንዘብ በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ ፩(መ) መሠረት የሚከተለውን ውሳኔ አስተላልፏል።

የፓሪሱን ውሳኔ የደገፉት አምስቱ ድርጅቶች ከዛሬ መጋቢት 23 ቀን 1985 ዓ.ም ጀምሮ ከምክር ቤት አባልነታቸው እንዲወገዱ፤ ሆኖም በውሳኔው ቅሬታ ያላቸው ካሉ በሰባት ቀናት ውስጥ ቅሬታቸውን ለምክር ቤቱ ማቅረብ እንደሚችሉ ተወስኗል።

MR NEGEDE